District of Columbia
Office of the State Superintendent of Education

# OSSE የትምህርት አስተዳደር ስርዐት (OSSE LMS)

## የተደራሽነት መመሪያ

ሜይ 2023

# ማውጫ

**መግቢያ** ..... **3**

**OSSE LMSን ማግኘት** ..... **3**

  ***ነጠላ የውል (SSO) መግቢያ ማስረጃዎችን ማቋቋም*** ..... ***3***

  ***ወደ OSSE LMS መግባት*** ..... ***6***

**መላ መፈለግ** ..... **8**

**በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች** ..... **9**

# መግቢያ

ይህ መመሪያ ኦፊስ ኦፍ ዘ ስቴት ሱፐርኢንተንደንት ኦፍ ኤጁኬሽን የትምህርት አስተዳደር ስርዐት (OSSE LMS)፣ አዲሱን ለዲሲ የቅድመ ልጅነት የሰው ሃይል አዲሱን የሙያዊ እድገት ስልጠና መድረክን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል የሚገልጽ መመሪያ ሆኖ ያገለግላል። የOSSE LMS አላማ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎችን፣ የህጻናት እንክብካቤ አቅራቢዎችን እና የአስተዳደር ሰራተኞችን በተሳካ የትምህርት እና የእድገት ስርዐት ማጎልበት ነው። OSSE LMS የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ይዘትን በተማከለ ቦታ የሚያደራጅ ሲሆን፣ ለሙያዊ ትምህርት ያልተገደበ መዳረሻ ያቀርባል እንዲሁም የተጠቃሚውን እድገት ተከታትሎ ያቆያል። የ OSSE LMS የሙያዊ እድገት መረጃ ስርዐትን (PDIS) (dcpdis.org) ይተካል። ከጁን 19, 2023 በስራ ላይ የሚውል ሲሆን፣ PDIS ከዚህ በኋላ ተደራሽ አይሆንም።

# OSSE LMSን ማግኘት

ይህ ክፍል OSSE LMSን ለማግኘት ደረጃ በደረጃ ያለውን ሂደት ያብራራል።

## ነጠላ የውል (SSO) መግቢያ ማስረጃዎችን ማቋቋም

በOSSE ነጠላ የውል (SSO) መግቢያ ማስረጃዎችን በማዘጋጀት፣ ተጠቃሚዎች ለሁሉም ተዛማጅ የOSSE ማመልከቻዎች መዳረሻቸውን በተሳካ መልኩ መያዝ ይችላሉ። ፈቃድ ባለው የዲሲ የልጅ እድገት ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ሁሉም ሰራተኞች በመጀመሪያ የSSO መግቢያ ማስረጃዎቻቸውን በሚከተሉት ደረጃዎች በማዘጋጀት የOSSE LMS መድረከን ማግኘት ይችላሉ።

1. የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ ይጎብኙ፦ osse.pl.powerschool.com። ከታች ያለውን ሰማያዊ “አሁን ይመዝገቡ” የሚል ማስፈንጠሪያ ጠቅ ያድርጉ።




2. ከታች ያለው ቅጽ ይታያል። የQuorum (quorumlearning.com) መለያ ካለዎት፣ በመጀመሪያው ሳጥን ውስጥ ከዚያ መለያ ጋር የተገናኘውን የኢሜይል አድራሻ ያስገቡ። የQuorum መለያ ከሌለዎት፣ ከPDIS መለያዎ (dcpdis.org) ጋር የተገናኘውን የኢሜይል አድራሻ ያስገቡ። የQuorum ወይም የPDIS መለያ ከሌለዎት ወይም መለያዎች እንዳለዎት እርግጠኛ ካልሆኑ፣ እባክዎ እርዳታ ለማግኘት የቅድመ ልጅነት ትምህርት (ECE) የእገዛ ዴስክን በECEhelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903 ያነጋግሩ።




3. የኢሜይል አድራሻዎን ካስገቡ በኋላ፣ “የማረጋገጫ ኮድ ላክ” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ። የማረጋገጫ ኮድ ወዳስገቡት የኢሜይል አድራሻ እንደተላከ መልዕክት ይመጣል። “DCGov – B2C – OSSE መለያ ኢሜይል ማረጋገጫ ኮድ” የሚል የርዕስ ያለው ኢሜይል መላኩን በኢሜይል የመልዕክት ሳጥንዎ ውስጥ ያረጋግጡ።




4. ኮዱን ከኢሜይል መልዕክት ከ”ኢሜይል አድራሻ” ሳጥን በታች ወደሚታየው የ “ማረጋገጫ ኮድ” ሳጥን ይቅዱ። “ኮድ አረጋግጥ” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።




5. አንድ ጊዜ የኢሜይል አድራሻዎ ከተረጋገጠ በኋላ፣ ሁለቱን የይለፍ ቃል መስኮች ብቻ ይሙሉ፣ ከዚያም "ፍጠር" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ። በ"ስም አሳይ"፣ "የተሰጠ ስም፣" ወይም "የአያት ስም" መስኮች ውስጥ ምንም ነገር ማስገባት አያስፈልግዎትም። ከQuorum መለያዎ ጋር የተገናኘው የኢሜይል አድራሻ (ወይም የ Quorum መለያ ከሌለዎ የPDIS መለያ) አስቀድሞ በስርዐቱ ውስጥ አለ። ከQuorum ወይም PDIS መለያዎ ጋር የተገናኘውን የተሳሳተ ኢሜይል እንዳስገቡ እስካላመኑ ድረስ "ኢሜይል ቀይር" የሚለውን አይጫኑ።




a. የኢሜይል አድራሻዎ በስርዐቱ ውስጥ ከሌለ፣ ከዚህ በታች ያለውን መልዕክት ያገኛሉ። ድጋፍ ለማግኘት እባክዎ የ OSSE ECE የእርዳታ ዴስክን በ ECEhelpdesk@dc.gov ወይም በ(202) 478-5903 ያነጋግሩ።




6. አንድ ጊዜ የእርስዎ SSO ማስረጃዎች ካቋቋሙ በኋላ፣ ስርዐቱ ወደ እርስዎ OSSE LMS መነሻ ገጽ ይወስድዎታል።




# ወደ OSSE LMS መግባት

1. አንድ ጊዜ የእርስዎን SSO ማስረጃዎች ካቋቋሙ በኋላ፣ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ በመንብኘት ወደ OSSE LMS መለያዎ ይግቡ፦ osse.pl.powerschool.com። በላይኛው ቀኝ ላይ “የOSSE ተጠቃሚ” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።




2. በሚታየው ቅጽ ውስጥ፣ የእርስዎን የSSO ማስረጃዎችን ለማቋቋም የተጠቀሙትን የኢሜይል አድራሻ ያስገቡ፣ ከዚያም “ቀጣይ” የሚለውን አዝራር ጠቅ ያድርጉ።




ቀጥሎ በሚታየው ቅጽ ውስጥ፣ የይለፍ ቃልዎን ያስገቡ እና “ግባ” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።




3. ስርዐቱ ወደ OSSE LMS መነሻ ገጽዎ ይወስድዎታል።




# መላ መፈለግ

ለጥያቄዎች ወይም ቴክኒካዊ እርዳታ፣ የECE እገዛ ዴስክን በ ECEhelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903 ያነጋግሩ።

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

- **የOSSE LMS አላማ ምንድን ነው?** የOSSE LMS አላማ አስተማሪዎችን፣ አቅራቢዎችን እና የአስተዳደር ሰራተኞችን በተሳካ ትምህርት እና የእድገት ስርዐት ማጎልበት ነው። OSSE LMS የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ይዘትን በተማከለ ቦታ የሚያደራጅ ሲሆን፣ ለሙያዊ ትምህርት ያልተገደበ መዳረሻ ያቀርባል እንዲሁም የተጠቃሚውን እድገት ተከታትሎ ያቆያል። ለዲሲ የቅድመ ልጅነት የስራ ሃይል፣ OSSE LMS PDISን (dcpdis.org) የሚተካ ይሆናል።

- **OSSE LMSን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?** OSSE LMSን በosse.pl.powerschool.com ላይ ማግኘት ይቻላል። ለመግባት፣ ተጠቃሚዎች መጀመሪያ የSSO ማስረጃዎቻቸውን ማቋቋም አለባቸው። መመሪያዎችን ለማግኘት ገጽ 3ን ይመልከቱ።

- **OSSE SSO ማቋቋምን ለምን ይጠቀማል?** በOSSE የመግቢያ ማስረጃዎች ላይ ነጠላ የውል መግቢያ በመፍጠር፣ ተጠቃሚዎች የሁሉም ተዛማጅ የOSSE ማመልከቻዎች መዳረሻቸውን በተሳካ መልኩ መያዝ ይችላሉ።

- **ለSSO ማስረጃዎቼ ምን አይነት የኢሜይል አድራሻ መጠቀም አለብኝ?** የQuorum (quorumlearning.com) መለያ ካለዎት፣ በመጀመሪያው ሳጥን ውስጥ ከዚያ መለያ ጋር የተገናኘውን የኢሜይል አድራሻ ያስገቡ። የQuorum መለያ ከሌለዎት፣ ከPDIS መለያዎ (dcpdis.org) ጋር የተገናኘውን የኢሜይል አድራሻ ያስገቡ። የQuorum ወይም የPDIS መለያ ከሌለዎት ወይም መለያዎች እንዳለዎት እርግጠኛ ካልሆኑ፣ እባክዎ እርዳታ ለማግኘት የቅድመ ልጅነት ትምህርት (ECE) የእገዛ ዴስክን በECEhelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903 ያነጋግሩ።

- **የSSO ማስረጃዎቼን እንዴት ማቋቋም እችላለሁ?** osse.pl.powerschool.comን ይጎብኙ እና “አሁን ይመዝገቡ” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ። በዚህ መመሪያ ገጽ 3 ጀምሮ የተሟሉ መመሪያዎች ይገኛሉ።

- **አንድ ጊዜ የSSO ማስረጃዎቼን ካቋቋምኩ በኋላ፣ OSSE LMSን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?** ወደ OSSE LMS መድረሻ ገጽ በosse.pl.powerschool.com ያስሱ። የSSO ማስረጃዎችዎን በመጠቀም ይግቡ። በዚህ መመሪያ ገጽ 6 ጀምሮ የተሟሉ መመሪያዎች ይገኛሉ።

- **በOSSE LMS ችግር ካጋጠመኝ የማነጋግረው ማንን ነው?** የኢሜይል አድራሻዎ ስላልታወቀ የመግቢያ ማስረጃዎችን ማቋቋም ካልቻሉ፣ ወይም በ OSSE LMS ላይ ሌላ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎ እርዳታ ለማግኘት የECE እገዛ ዴስክን በECEhelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903 ያነጋግሩ።